# የአሲምባ ድረ-ገጽ የትዝብት አምድ ቁጥር ፬

## ታምራት ላይኔ ስለ ወቅታዊው የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታዎችና ብሄራዊ እርቅ ዙርያ? ሰው ጠፋ? ወይንስ ውዥንብሩ ተጧጧፈ?

## ሐዋርያ አንቺም እንደ ሌላው? ያ ትውልድ የቤት ሥራውን ያጠናቅቅ በሚል ርዕስ የተጻፈው እንዲያው ለማን ነው?

1. ታምራት ላይኔ ስለ ወቅታዊው የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታዎችና ብሄራዊ እርቅ ዙርያ? በአውስትራሊያ የሚገኘው ኤስ ቢ ኤስ ራዲዮ ጣቢያ በዲያስፖራ ያለውን ሕዝብ የማምታት ሥራውን በመቀጠል ሰሞኑን ደግሞ ታምራት ላይኔን ይዞልን ቀርቦአል። አዘጋጁ አሁን እየተነሳሳ ያለው የሕዝብ አምጽ ወያኔንና ተለጣፊዎችን ሁሉ ጠራርጎ የሚሄድ መሆንኑ ሊረዳው የሚችል ችሎታ እንደሌለው ለብዙዎቻችን በደርግ ጊዜ የነበረውን ለምናውቅ ግልጽ ነው። እየተነሳሳ ያለው አመጽ ወያኔንና ተለጣፊዎቹን እንዲሁም የዘር ፖለቲከኞችን ጠራርጎ እንደሚያልፍ ጥርጥር የለውም። ታምራት ላይኔ ራሱ ወንጀለኛና ተጠያቂ ነው እንለዋለን። (https://www.youtube.com/watch?v=GIYk2kHJkzc )

   ለነገሩ ታምራት ብቻም አይደለም። ብዙ እየታዘብንና ገና ብዙም ያሳየናል። ወያኔን ጠጋግኖ ለማስቀጠል የሚደረገው ውዥንብር ከመቼውም የበለጠ ተጧጥፏል። ምዕራባውያንም ከወያኔ በኋላ ጥቅማቸውን ሊያስጠብቁ የሚችሉ ደካሞችን ከማካከላችን መሪ ሊያወጡልን እየተራወጡ ነው። እኛም ነቅተናል እንላለን። ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም የሚለውን የ 1966ቱን ሕዝዝባዊ አመጻ ድምጽም እናስታውሳቸዋለን። እየተነሳ ያለው ሕዝባዊ አመጽ ወያኔን፣ ተለጣፊዎቹን፣ አስመሳዮቹን፣ ዘረኛ ፖለቲከኞችን ሁሉ ጠራርጎ በኢትዮጵያዊነት ጥላ ሥር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን መሥርቶ ለማለፉ ለአንድ አፍታም አንጠራጠርም!

ይህች ልዩ አምድ በአሁኗ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ የወያኔን ሥርዓት አንኮታኩቶ ለመጣል ከመቼዎም የበለጠ የተነሳሳበትና ትግሉንም በሕብረ-ብሔራዊ መልክ መቅረጽን የተረዳበት ለመሆኑ በቅርቡ በሰሜን ኢትዮጵያ የተካሄዱት ሰላማዊ ሰልፎችና ሕዝባዊ አመጾች ያሳያሉ። ይህም የትግል አቅጣጫ ወያኔንና ደጋፊዎቹን፣ ተለጣፊዎቹን አስደንግጧል። የሕዝብ አመጻ እየገፋ በሚመጣበት ጊዜ ደግሞ የኃይል ሚዛን ለውጥ ስለሚኖር ያንን ለመገደብ ወይም ጠልፎ ለራስ ለማድረግ በወያኔም በኩል በሁሉም የሕዝብን ድምፅ እያሰማ የሚመጣ ስብስብና ቡድን እንደ አሸን የሚፈላበት ወቅት ስለሆነ የአሲምባ አንባቢያን ግንዛቤን እንዲያገኙ አለፍ አለፍ ብለን ከድህረ-ገፆች አካባቢና ከሌሎችም ያገኘናቸውን አጠር ካለ አስተያየት ጋር የምናቀርብበት አምድ ይሆናል።

2. ሐዋርያ አንቺም እንደ ሌላው ? ያ ትውልድ የቤት ሥራውን ያጠናቅቅ በሚል የተጻፈው ምልዕክት ለማን ነው? [http://assimba.org/Articles/Hawaria_Special_Edition00782.pdf](http://assimba.org/Articles/Hawaria_Special_Edition00782.pdf)

*"….በህይወት ያሉ የዚያ ትውልድ አባላት ሲታገሉ ከወደቁ ሙታን ጓዶቻቸው ጋር ሆነው የጀመሩትን እንዲጨርሱ ታሪክ ዛሬም እንደገና ሌላ እድል ሰጥታቸዋለች። በዚያ ትውልድ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ግንዛቤ ያለፉ ዜጎች የተቀሰቀሰው ሕዝባዊ እምቢተኝነት መስመር ይዞ እንዲተምና ወደ ዘላቂ ግብ እንዲያነጳጽር አጣዳፊ መልስ ይሰጡ ዘንድ ወቅቱ ቢያሉበት ንቁጣ የግድ ይላቸዋል…."*

ከዚህ በላይ ያለውን አጣቅሳ **እንደ መስቀል ወፍ ብቅ** ያለችውን የሐወርያ ልዩ ዕትም ላነበብን ዝቅ ብላ ደግሞ ከታች በጥቅስ ውስጥ ያስቀመጥነውን ዓይነት አስተያየት ስታቀርብ ብዙዎቻችን ታዋቂዋ ሐዋርያን እንድንታዘባት ሲያደርገን መልዕክቷ የተምታታ፣ ከድርጅቱ ውስጥ በተላያዩ ምክንያት ወጥተን ከውጭ ለተቀመጥን ድርጅቱን እንቀላቀልና ከሕዝቡ ትግል ጎን እንሰለፍ ሳይሆን ያንኑ ያለፈበት የነፈሰበት ዓይነት የተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ዓይነት ከውጭ ሆነን በድርጅቱና ትግሉን ያስቀጠሉት ላይ እጣታችንን እየቀሰርን ቁም ስቅላቸውን ከምናሳያቸውና ስንሳለቅባቸው፣ አንዳንዶቻችንም ከወያኔ በባሰ የዚያን ታጋይ ትውልድ መሠረታዊ ዕምነት የሚጻረር ማፈሪያ ሆነን በዘሩም በሁሉም ዓይነት የተግማማ ፖለቲካ ስንጨማለቅ የኖርነው፣ ትክክለኞች ነን ወይንም ነበርን ዓይነት ንትርክ ለማስቀጠል መሞከሯ አስገርሞናል፣ አሳዝኖናልም። የሕዝቡ ትግል ሞቅ፣ ገንተር ሲል ሐዋርያ ለምን በዚህ ልታነታርከን ፈለገች ብለን እንድንጠይቅም ሆነናል።

*"……በትግል ላይ ካሉት ወገኖች ጋር ፈጣን ግንኙነት እየፈጠሩ ንጹህ ውይይት በመጀመር ጊዜና ቦታ መርጠው አጠቃላይ የመልሶ መጠናከሪያ ጉባኤ ማካሄድና ለሀገሪቱ አንድ ጠንካራ አማራጭ የፖለቲካ ፓርቲ ማመቻቸት የረጅሙ ትግል መሰብሰቢያና ማሰሪያ ይሆናል ብሎ መተንበይ ይቻላል….."*

*ከዚህ በላይ ያለውን ላነበብን ደግሞ ሁሉ ነገር የተገላቢጦሽ ሆነብን። ሳይሉን በራሳችን ፈቃድ ድርጅቱንና ትግሉን ጣጥለን ጭራችንን ቆልፈን ወደ ምዕራቡ ዓለም የሄድነው ሁላ፣ አንዳንዶቻችንም የወያኔ ተለጣፊ ወይም የዘር ፖለቲካ የፈተፈትን ተመልሰን ለመቀላቀል እስከ ዛሬ ትግሉን ያስቀጠሉት ወገኖችን ዕምነት በመገንባት፣ ድርጅቱ ውስጥ አስገቡንና ትግሉን እንቀጥል ሳይሆን በምን የሞራል ብቃታችን እንደሆነ ጉባኤ ይጠራልን እንደምንል ሊገባን ከቶውንም አይቻለንም። አዬ ሐወርያ ደህና ሰው ሲበላሽ… የሚለውን ያስታውሰናል። ድርጅቱን ለማስተካከልም ሆነ ለማንኛውም ጉዳይ ጉባኤ ይጠራም የሚለው ክፍል እኮ እዚያው በድርጅቱ*

ይህች ልዩ አምድ በአሁኗ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ የወያኔን ሥርዓት አንኮታኩቱ ለመጣል ከመቼዎም የበለጠ የተነሳሳበትና ትግሉንም በሕብረ-ብሔራዊ መልክ መቅረጽን የተረዳበት ለመሆኑ በቅርቡ በሰሜን ኢትዮጵያ የተካሄዱት ሰላማዊ ሰልፎችና ሕዝባዊ አመጾች ያሳያሉ። ይህም የትግል አቅጣጫ ወያኔንና ደጋፊዎቹን፣ ተለጣፊዎቹን አስደንግጧል። የሕዝብ አመጻ እየገፋ በሚመጣበት ጊዜ ደግሞ የኃይል ሚዛን ለውጥ ስለሚኖር ያንን ለመገደብ ወይም ጠልፎ ለራስ ለማድረግ በወያኔም በኩል በሁሉም የሕዝብን ድምፅ እያሰማ የሚመጣ ስብስብና ቡድን እንደ አሸን የሚፈላበት ወቅት ስለሆነ የአሲምባ አንባቢያን ግንዛቤን እንዲያገኙ አለፍ አለፍ ብለን ከድህረ-ገፆች አካባቢና ከሌሎችም ያገኘናቸውን አጠር ካለ አስተያየት ጋር የምናቀርብበት አምድ ይሆናል።

*ውስጥ ተቀምጦ፣ የድርጅቱን መርሃ ግብር አክብሮ ለድርጅቱ ታማኝ ሆኖ እዚያው ከውስጥ ሆነ ሳለ ነው እንጂ ጣጥሎማ ከወጡ በኋላ ያንን ሁሉ መብት ወርውሮ የሄደ ለመሆኑ እውን ሐዋርያ ይሄንን ሳትገነዘብ ቀርታ ወይስ ወዴት ወዴት እኮ? ሁሉም በመርህ ሲሆን ጥሩ ነው። አሲምባ በቅርቡ ድርጅቱ የተቀመጠበትን ጉባኤ ረግጠው የወጡትንና በየሚዲያው ያዙን ልቀቁን ዛሬም ድረስ የድርጅቱን ስም ይዘው የሚንዘላጠሉትን የምናወግዘው እኮ አንስተን ነበር ያሉት ጥያቄ ትክክል ውይም ስህተት ነው በማለት ሳይሆን ችግራችሁን ሊፈታ የተቀመጠውን ጉባኤ አስጨርሳችሁ አብዛኛው የሚወስነውን ለመስማት እንኳ ለምን አልፈለጋችሁም በሚል ነበር። አሁንም ትግሉን ከድርጅቱ ጋር እንቀጥል እያሉ ከሆነና ሐዋርያም ያንን እያቀረበች ከሆነ መንገዱ አንድና አንድ ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው። ያ አካሄዳቸው ትክክል እንዳልሆነ በመጥቀስና እስካሁን ድርጅቱ ላይ ያደረሱትን ጉዳት በማመን የአባላቱን ታማኝነት በማግኘት የሚቀላቀሉበትን መንገድ በማመቻቸት በድርጅቱ ውጥጥ ካሉት ጋር ተቀላቅሎ ከሕዝቡ ትግል ጎን ሳይመሽ መቀላቀል መፈለግ ወይንም አለመገለግ ጉዳይ ነው።*

*"…….ሕዝባዊ ፍቅራቸውና ተቆርቋሪነታቸው እንደታተመ ያለ ለመሆኑ ማስረጃ ከሚሆኑት ብዙ ክስተቶች አንዱ በውጭ ሀገር ላለፉት 33 ዓመታት በየዓመቱ በሚካሄደው የኢትዮጵያዊያን የሰሜን አሜሪካ ስፖርት ሳምንታዊ በዓል ላይ የኢሕአፓ የድሮ አባላት ላንዴም ሳያቋርጡ በየዓመቱ የሚያደርጉትን ናፍቆታዊ ግንኙነትና የሃሳብ ልውውጥን መመልከት ይበቃል……እንደ ድርጅቱ ትልቅነትና ሚና ኢሕአፓን በየደረጃው በሃላፊነት መርተናል ወይም እንመራለን የሚሉ ወገኖች ለትግሉ መርገብና አልባሌነት ትልቁን የዝሆን ድርሻ ይጋራሉ ተብሎ ሊታመን ይችል ይሆናል። ይህ የታሪክ ሃላፊነት የሚያስደነግጣቸው ካሉ፤ የዚያ ህልመኛ ትውልድ መሪ የነበሩና የሆኑ አባቶችንና እናቶችን ሕዝባችን ዛሬም ከመቸውምጊዜ በበለጠ ይፈልጓቸዋልና አስበውበት ከፈጠኑ እዳቸውን ሊወጡ ይችላሉ። እየመሸ ነውና ፀሐይ ሳትጠልቅ የሆነውን ሁሉ ለታሪክ ትተው እርስ በርሳቸው በይቅርታ ከተጎናበሱ፤ የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት ባደረገና ዓለም አቀፍ ሁኔታውን ባገናዘበ መልኩ ድርጅታቸውን ኢሕአፓን ከሰመመን እንቅልፍ መቀስቀስ ከቻሉ ከታሰበው የሚያደርስ በቂ ጊዜ አለ።"*

*ከዚህ በላይ ያለውን ላነበብን ደግሞ በሐዋርያ ላይ ትዝብት ብቻ ሳይሆን አዝነናል። እንዴ? 33 ዓመት ሙሉ በያመቱ ፓርቲ ስናደርግ እኮ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንደራጅና እንታገል የሚለውን እንኳን እንተወውና ለራሳችን መረዳጃ ማሕበር ወይም እድር መሳይ እንኳን አቋቋምን? ከ33ቱ ዓመት ለምናስታውሳቸው ጓዶቻችን መታሲቢያ ወይንም የምናውቃቸውን ጧሪ ያጡ ቤተ ሰቦቻቸውን እንርዳ ብለን የአንዱን ዓመት ፓርቲ ወጪ ገንዘብ እንላክ አልን? ለይስሙላ 33 ዓመታት በሙሉ እየተሰበሰቡ ከንፈር መምጠጡ ምን ይሠራል? ደግሞም እንነገር ከተባለ እኮ እኛ 33 ዓመት እየተሰባሰብን ስንፈነጭ ከኛው ጋር የነበሩ ጓዶቻችን ትግሉን አስቀጥለው መስዋዕትነት እየከፈሉ መሆኑን እናውቃለን ለመሆኑ? እንፀጋዬ የመሳሰሉት እኮ በወያኔ ካልፍርድ ተገድለዋል። ብዙዎቹም ሕይወታቸውን ሰጥተዋል። አላወቅነውም እንጂ ትግሉን ያስቀጠሉት እኮ ናቸው እኛም ኢሕአፓ ነበርን እያልን እንድንመጻደቅ ያደረጉን። ኢሕአፓ እስከ ዛሬይቷ ቀን ድረስ በትግል ላይ ያለ ድርጅት ነው ብለን እንኳ ብዙዎቻችን አናምንም። አይገርምም? በሰመመን እንቅልፍ ውስጥ ያለነውና መንቃት ያለብን ሐዋርያ 33 ዓመታት ቆጥራ ያቀረበችን የድሮ ኢሕአፓ አባላት ነበርን የምንለው ነን። ለነገሩ ሐወርያ ለመሆኑ ከትግሉ ውጪ ያሉ ሁሉ ያ በትግሉ ውስጥ የነበረንን ዕምነት ይዘን አለን ነው የምትለን? ከወያኔ፣ ከዘረኝነቱም፣ በያይነቱና በየአቅጣጫው እንዳለን ተገንዝባ ይሆን? ለማንኛውም ሐዋርያ ካነሳችው በማለት ብዙ ሊጠቀሱ ከሚችሉት*

ይህች ልዩ አምድ በአሁኗ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ የወያኔን ሥርዓት አንኮታኩቱ ለመጣል ከመቼዎም የበለጠ የተነሳሳበትና ትግሉንም በሕብረ-ብሔራዊ መልክ መቅረጽን የተረዳበት ለመሆኑ በቅርቡ በሰሜን ኢትዮጵያ የተካሄዱት ሰላማዊ ሰልፎችና ሕዝባዊ አመጾች ያሳያሉ። ይህም የትግል አቅጣጫ ወያኔንና ደጋፊዎቹን፣ ተለጣፊዎቹን አስደንግጧል። የሕዝብ አመጻ እየገፋ በሚመጣበት ጊዜ ደግሞ የኃይል ሚዛን ለውጥ ስለሚኖር ያንን ለመገደብ ወይም ጠልፎ ለራስ ለማድረግ በወያኔም በኩል በሁሉም የሕዝብን ድምፅ እያሰማ የሚመጣ ስብስብና ቡድን እንደ አሸን የሚፈላበት ወቅት ስለሆነ የአሲምባ አንባቢያን ግንዛቤን እንዲያገኙ አለፍ አለፍ ብለን ከድህረ-ገፆች አካባቢና ከሌሎችም ያገኘናቸውን አጠር ካለ አስተያየት ጋር የምናቀርብበት አምድ ይሆናል።

# የአሲምባ ድረ-ገጽ የትዝብት አምድ ቁጥር ፬

*ጥቂቶቹን አውጥተን ለትዝብት አምድ አቀረብን እንጂ ብዙም ብዙም ማለት ይቻል ነበር።*

*የአሲምባ ድረ-ገጽ በኢሕአፓ ውስጥ ትግሉን ላስቀጠሉ ወገኖች ከፍተኛ አክብሮት ያለው ሲሆን፣ የዚያን ትውልድ አርማ ይዘው እስከዛሬ ትግሉን ማስቀጠላቸውና ለከፈሉት መስዋዕትነት ምስጋና የሚገባ ለነሱ ስለሆነ ሁሌም እንኮራባቸዋለን። ዛሬ ከእንቅልፋችን ተነስተን ትግሉን ለመቀጠል ደግሞ በኢሕአፓ ውስጥ የሚከለክለን የለምና ብዙ ምክንያት ሳንደረድር ፍላጎቱ ካለ ለኛው ሳይመሽብን በቶሎ እንቀላቀል። ድርጅቱን መቀላቀል ባንችል ደግሞ ጥሩ ደጋፊ እንሁን። ካለዚያ እንዲያው ዝምምምምም። ለዕውነተኞቹ ኢሕአፓዎችማ ላለፉት 44 ዓመታት ለኢትዮጵያን ሁሉ እንዳ አባቶቻችን ዋርድያ እንደቆሙልን ነው።*

የኢሲምባ ድረ-ገጽ አዘጋጅ

ኢሕአፓ ለዘለዓለም ይኑር!

ድሮ ኢሕአፓ ነበርን የምንል ብዙ ምክንያት ሳናበዛ በምንችለው ኢሕአፓን እንርዳ!

ኢትዮጵያዊነት ያለጥርጥር በትግላችን ያቸንፋል።

ይህች ልዩ አምድ በአሁኗ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ የወያኔን ሥርዓት አንኮታኩቱ ለመጣል ከመቼዎም የበለጠ የተነሳሳበትና ትግሉንም በሕብረ-ብሔራዊ መልክ መቅረጽን የተረዳበት ለመሆኑ በቅርቡ በሰሜን ኢትዮጵያ የተካሄዱት ሰላማዊ ሰልፎችና ሕዝባዊ አመጾች ያሳያሉ። ይህም የትግል አቅጣጫ ወያኔንና ደጋፊዎቹን፣ ተለጣፊዎቹን አስደንግጧል። የሕዝብ አመጻ እየገፋ በሚመጣበት ጊዜ ደግሞ የኃይል ሚዛን ለውጥ ስለሚኖር ያንን ለመገደብ ወይም ጠልፎ ለራስ ለማድረግ በወያኔም በኩል በሁሉም የሕዝብን ድምፅ እያሰማ የሚመጣ ስብስብና ቡድን እንደ አሸን የሚፈላበት ወቅት ስለሆነ የአሲምባ አንባቢያን ግንዛቤን እንዲያገኙ አለፍ አለፍ ብለን ከድህረ-ገፆች አካባቢና ከሌሎችም ያገኘናቸውን አጠር ካለ አስተያየት ጋር የምናቀርብበት አምድ ይሆናል።